<u>የአላህ እዝነት</u>

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን! የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሰላም ከሁላችሁ ጋር ይሁንና እንደምን ሰነበታችሁ ወንድም እህቶቼ? ሙስሊም ወገኖች እንደምን አላችሁ? ዛሬ አምላካችን እግዚአብሔር ልባችንን ከፍቶ ቢገልጽልን አንድ እጅጉን ወሳኝ የሆነ ነጥብ የምናነሳ ሲሆን በርዕሱ ላይ እንዳያችሁት የአላህ ራህመት ወይም እዝነት ይሰኛል።

አላህ አዛኝ ሩህሩህ እየተባለ (ግማሹ ከጠፋው ከሱራ 9 ውጪ) በየሱራዎቹ መግቢያ ሆኖ የሚያገለግል ቃልና የአላህ ሲፋት (ባህርይ) ሲሆን ከኢስላም ወገኖቻችን አፍም አይጠፋም። አራሂም የሚለው የአላህ ስም ከ99ኙ የሚካተትና በጣም ወሳኙ የአላህ ስም ሲሆን ሙስሊሞች ደጋግመው በማለት የአላህን ምህረት የሚለምኑበት በዕለት ተዕለት አምልኮ ውስጥ ከፍተኛ ጥቅም ያለው ቃል ነው። ታዲያ ይህ የአላህ በጣም ጠቃሚው ሲፋት ያልተለወጠ የባህርይው የሆነ ወይስ ከጊዜ በኋላ የመጣና ፍጡር ነው? እዝነቱ ከጥንትም ጀምሮ የባህርይው ሆኖ ካልነበረስ ምንን ያመለክታል? ፈጣሪ ያልነበረውንና እንግዳ ባህርይን ለብሶ እንዲታወቅለት በየአያው ለማለት በሚያስችል ሆኔታ ማስተዋወቁ ምንን ያመላክታል? (ስሙ ወይም አራህማን የሚለው ስም ከዬት መጣ የሚለውን በደንብ ማዬት ለሚፈልግ ሰው “የአላህ ማሕጸን” የተሰኘውን ጽሑፌን እንዲያነቡ እመክራለሁ)። እስኪ ከዚህ በመቀጠል መጻሕፍቱ በዘመነኛ ኡስታዞች ሳይቆነጻጸሉ ቀጥታ ከምንጮቹ እንይ።

> عَنْ ،الْمَقْبُرِيِّ سَعِيدٍ أَبِي بْنِ سَعِيدِ عَنْ ،عَمْرٍو أَبِي بْنِ عَمْرِو عَنْ ،الرَّحْمَنِ عَبْدِ بْنُ يَعْقُوبُ حَدَّثَنَا ،سَعِيدٍ بْنُ قُتَيْبَةُ حَدَّثَنَا مِائَةَ خَلَقَهَا يَوْمَ الرَّحْمَةَ خَلَقَ اللَّهَ إِنَّ " يَقُولُ وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولَ سَمِعْتُ قَالَ ـ عنه الله رضى ـ هُرَيْرَةَ أَبِي عِنْدَ الَّذِي بِكُلِّ الْكَافِرُ يَعْلَمُ فَلَوْ ،وَاحِدَةً رَحْمَةً كُلِّهِمْ خَلْقِهِ فِي وَأَرْسَلَ ،رَحْمَةً وَتِسْعِينَ تِسْعًا عِنْدَهُ فَأَمْسَكَ ،رَحْمَةٍ النَّارِ مِنَ يَأْمَنْ لَمْ الْعَذَابِ مِنَ اللَّهِ عِنْدَ الَّذِي بِكُلِّ الْمُؤْمِنُ يَعْلَمُ وَلَوْ ،الْجَنَّةِ مِنَ يَيْأَسْ لَمْ الرَّحْمَةِ مِنَ اللَّهِ ."

Narrated Abu Huraira:

> I heard Allah's Messenger (ﷺ) saying, Verily Allah created Mercy. The day He created it, He made it into one hundred parts. He withheld with Him ninety-nine parts, and sent its one part to all His creatures. Had the non-believer known of all the Mercy which is in the Hands of Allah, he would not lose hope of entering Paradise, and had the believer known of all the punishment which is present with Allah, he would not consider himself safe from the Hell-Fire."

Sahih al-Bukhari, 6469

In-Book Reference: Book 81, Hadith 58

USC-MSA web (English) reference: Vol. 8, Book 76, Hadith 476 (deprecated numbering scheme)

እንደምናየው የአላህ ምህረት ፍጡር ሲሆን ቁጣው ግን የባህርይው ነው ምክንያቱም ዓለምን ሳይፈጥር ገና ዝምብሎ ይበሳጭ ነበርና። እስኪ እጅግ ከበዙት ሷሂህ ሃዲሳት የተወሰኑትን እንመልከት

Hadith

> ،اللَّيْثُ حَدَّثَنَا ،قُتَيْبَةُ حَدَّثَنَا ،هُرَيْرَةَ أَبِي عَنْ ،أَبِيهِ عَنْ ،عَجْلاَنَ ابْنِ عَنِ وسلم عليه الله صلى اللَّهِ رَسُولِ عَنْ " قَالَ غَضَبِي تَغْلِبُ رَحْمَتِي إِنَّ نَفْسِهِ عَلَى بِيَدِهِ كَتَبَ الْخَلْقَ خَلَقَ حِينَ اللَّهَ إِنَّ قَالَ أَبُو عِيسَى هَذَا حَدِيثٌ حَسَنٌ صَحِيحٌ . غَرِيبٌ .

Abu Hurairah narrated that the Messenger of Allah (ﷺ) said:

"Verily, Allah when He created the creation, He wrote with His Hand concerning Himself, that: 'My mercy prevails over My wrath.'"

Sahih (Darussalam)

Jami` at-Tirmidhi, 3543

In-Book Reference: Book 48, Hadith 174

English Reference: Vol. 6, Book 45, Hadith 3543

Hadith

يَحْيَى بْنُ مُحَمَّدُ حَدَّثَنَا ،عِيسَى بْنُ صَفْوَانُ حَدَّثَنَا ،عَجْلاَنَ ابْنِ عَنِ ،أَبِيهِ عَنْ ،هُرَيْرَةَ أَبِي عَنْ ،اللَّهِ رَسُولُ قَالَ قَالَ ـ غَضَبِي سَبَقَتْ رَحْمَتِي الْخَلْقَ يَخْلُقَ أَنْ قَبْلَ بِيَدِهِ نَفْسِهِ عَلَى رَبُّكُمْ كَتَبَ " ـ وسلم عليه الله صلى . "

It was narrated that Abu Hurairah said:

"The Messenger of Allah said: 'Your Lord wrote for Himself with His Own Hand before He created the creation: "My mercy precedes My wrath."

Sahih (Darussalam)

Sunan Ibn Majah, 189

In-Book Reference: Introduction, Hadith 189

English Reference: Vol. 1, Book 1, Hadith 189

ከላይ ባሉት ሳሂህ ሃዲሳት እንዳየነው የአላህ እዝነት ፍጡር መሆኑን እና እነዚህ ምህረቶች 100 ክፍል አድርጎ እንደፈጠራቸው በማያሻማ ቃል ይናገራል። "ኢና አላሃ ኻላቃ አራህመታ Verily Allah created mercy በርግጥም አላህ ምሕረትን ፈጠረው" በማለት ግልልጽ ባለ አነጋገር አስቀምጦታል። ይህም እዝነት ፍጡር ነው ማለት አላህ በባሕርይው ብስጩ ምህረት የለሽ ጨካኝ በአጠቃላይ የምህረት ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች በሙሉ ነው ማለት ነው ምክንያቱም ምህረቱን ሳይፈጥረው ብስጩና ቁጡ እንደሆነ ከላይ ያስቀመጥናቸው ሳሂህ ሃዲሳት ምስክር ናቸውና። ፈጣሪ ፍጥረቱን ከመፍጠሩም ከፈጠር በኋላም ባህርይው ተለወጠ ወይንም አዲስ ባህርይን ባህርይው አድርጎ ኖረ ማለት በጣም ከባድ ነገር ነው። ሲቀጥልስ ከሙሉ ሲፋት አላህ መካከል ምህረቱ ተለይቶ ለምን ፍጡር ሆነ? ኽይሩል ማኪር መባሉ(አታላይነቱ)፣ አልፈታን መሆኑ(የሚፈትነው)፣ አዷር(ጎጂው) መባሉ ወዘተ ለምን ፍጡራን አልተባሉም? አላህ መልካም የሆነውን ምህረት ባህርይው ውስጥ ሳይኖር መጥፎ የሆኑት ማታለል፣ መጉዳት፣ መፈተን፣ ወዘተ ከጥንትም ጀምረው የባህርይው ሆነው አሉ ማለት አላህ በባህርይው ምህረት የለሽና መልካም ነገር የሌለው አያደርገውም? መልካም የሆኑትን ፈጥሮ ከተዋሃዳቸው በኋላ መልካም ቢባል የተገባው ነው በርግጥ ግን ደግሞ ከጥንትም ያልነበሩ ፍጡራን በመሆናቸው ባህርይው ከነሱ በተቃራኒ ያሉትን ነው ማለት ነው። በምሳሌ ነገሩን ለማስረዳት ያክል ውሾች ለምሳሌ አደንዛዥ እጽዋትን አነፍንፎ ማግኜትን ይማራሉ፣ በዚህ ጽሎታቸው ላይ ቆሞ በሁለት

እግር መሄድን ቢለምዱ ውሻነታቸው አይቀርም። Learned የሆነው behavior መጀመሪያ የነበረውን አጥፍቶ ማስብ የሚችሉ በሁለት እግር የሚራመዱ ሊላ ስም ያላቸው ፍጥረታት አያደርጋቸውም። አነፍናፊ በሁለት እግር ተራማጅ ውሾች ያደርጋቸዋል እንጂ ስለዚህ አላህም ምሕርቱን ፈጥሮት መሐሪ ሲባል ከጥንትም ስለነበረ ባሕርያዊ ስለሆነ ሳይሆነ ከጊዜ ብኋላ የመጣ በመሆኑ ነው(ምናልባት ሙስሊም ወገኖቼ እንድትረዱልኝ የምፈልገው ምሳሌው ጉዳዩን የበለጠ ያስረዳልኛል ብዬ መጠቅሜን እንጂ ሌላ የተደበቀ motive እንደሌለው ነው)። ታዲያ እነዚህ ሃሳቦች ሲነሱ ልክ እንደሌሎች ጉዳዮች የተለያዬ መልስ የሚሰጡ ቢሆንም አላህ 99ኙን ራሱ ጋር አስቅርቶ አንድ ክፍል የምትሆነውን ለፍጥረቱ ሰጣት ማለት ፍጥረታቱ እርስ በርሳቸው የሚተዛዘኑት አላህ በሰጣት በዚህች ምህረት ነው በማለት የተጻፈውን ቃል በመሰለኝና ደስአለኝ የሚያጣምሙ መምህራነ ሐሰት ኡስታዞች ይህች ምህረት ለፍጥረቱ ስለተሰጠች ነው እርስ በርሳችን በመተዛዘን የምንኖረው የሚል እጅግ በጣም አደገኛ መልስ ይሰጣሉ። በመጀመሪያ ደረጃ ለፍጥረቱ እንዲተዛዘኑ ሰጣት የሚል ሃሳቡም የለም! የሚለው ወአርሰላ ፊይ ኸለቂሂ ኩሊሂም ራህመቲ ዋሂዳሃ ነው ማለትም ከፈጠራቸው ምህረቶችም ውስጥ አንዷን ምህረት ላካት(አርሰላ) ነው። በዚህች ለፍጥረት በላካት ምህረት ነው ፍጥረታቱን የሚምራቸው። እሺ እነሱ በሚሉት እንሂድና አላህ በራሱ ዘንድ ያለውን ራህመት ለፍጥረቱ በመስጠቱ ምክንያት ፍጥረታቱ የአላህ ራህመት ተሳታፊ ናቸው ማለት ነው! ይህ ደግሞ ከ100% ውስጥ 1% አላህን በምህረቱ እንዲመስሉት ያደረጋቸው ሲሆን አምሳያ የለውም የሚለውን ትርክታቸውን አደጋ ውስጥ ይጥላል። በመሆኑም ይህ ወደ ፍጥረት የተላከቺው ምሕረት ፍጥረታቱ ሊተዛዘኑባት ነው የሚለውን ግምታችሁን ተዉትና ሌላ ሻል ያለ ውሸት ይዛችሁ ኑ (ከአላህ መክር ተሳተፉ በደንብ)። እስኪ እንደው ከገረመኝ ነገር ደግሞ ምሕረት መቆጠር የሚችል ነገር ነው እንዴ? ምሕረት አንድ ሁለት ተብሎ የማይቆጠር ባህርይ ሆኖ ሳለ 100 አደረጋት ማለት ምን አይነት ጭለላ ነው? ቁጣን፣ ፍቅርን፣ ጸብን፣ ጥላቻን፣ ብቀላን፣ ደግነትን፣ ወዘተርፈ መቁጠር እንደማይቻለው ሁሉ ምህረትም ባህርያዊ ግብር በመሆኑ Uncountable Attribute ነው። ስለዚህ 100 10 1 ወዘተ የማይባል ነውና ተቆጥሮ መቀመጡ እጅጉን አስገርሞናል።

እስኪ ምናልባት ሃዲስ ሲመጣ ከመሐመድ አስከሬን ቢሰሙት እንኳን ደኢፍ ነው ከማለት የሚመለሱ የማይመስሉት ሰዎች ምናልባት ከላይ ባዬነው ሳሂህ ሃዲስ ላይ ጌታችሁ በራሱ እጅ ምህረቴ ቁጣዬን በለጠች ብሎ ጻፈ የሚለውን ደግሞ በቁርአን እይታ እንይ እስኪ፦

የቤት እንስሳት ምዕራፍ አያ 12(6፡12)

> خَسِرُوا الَّذِينَ ۚ فِيهِ رَيْبَ لَا الْقِيَامَةِ يَوْمِ إِلَىٰ لَيَجْمَعَنَّكُمْ ۚ الرَّحْمَةَ نَفْسِهِ عَلَىٰ كَتَبَ ۚ لِلَّهِ قُل ۖ وَالْأَرْضِ السَّمَاوَاتِ فِي مَّا لِّمَن قُل يُؤْمِنُونَ لَا فَهُمْ أَنفُسَهُمْ
>
> «በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የማን ነው» በላቸው፡፡ (ሌላ መልስ የለምና) «የአላህ ነው» በል፡፡ **«በነፍሱ ላይ እዝነትን ጻፈ**፡፡ በትንሣኤ ቀን በእርሱ ጥርጥር የሌለበት ሲኾን በእርግጥ ይሰበስባችኋል፡፡ እነዚያ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩ ናቸው፤ እነርሱም አያምኑም፡፡

የቤት እንስሳት ምዕራፍ አያ 54(6፡54)

> وَإِذَا جَاءَكَ الَّذِينَ يُؤْمِنُونَ بِآيَاتِنَا فَقُلْ سَلَامٌ عَلَيْكُمْ ۖ كَتَبَ رَبُّكُمْ عَلَىٰ نَفْسِهِ الرَّحْمَةَ ۖ أَنَّهُ مَنْ عَمِلَ مِنكُمْ سُوءًا بِجَهَالَةٍ ثُمَّ تَابَ مِن بَعْدِهِ وَأَصْلَحَ فَأَنَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ

> እነዚያም በተአምራታችን የሚያምኑት (ወደ አንተ) በመጡ ጊዜ «ሰላም በእናንተ ላይ ይኹን:: **ጌታችሁ በነፍሱ ላይ እዝነትን ጻፈ**:: እነሆ ከእናንተ ውስጥ በስሕተት ክፉን ሥራ የሠራ ሰው ከዚያም ከእርሱ በኋላ የተጸጸተና ሥራውን ያሳመረ እርሱ (አላህ) መሓሪ አዛኝ ነው» በላቸው::

ከላይ ያሉት አያዎች በማያሻማ መልኩ ከሳሂህ ሃዲሳቱ ጋር ተስማምተው እንዳስቀመጡልን እዝነትን ወይም ምሕረትን በነፍሱ ላይ ጻፈ ይላል። ከተባ ዓሊ ነፍሲሂ አራህማታ በማለት ያስቀምጠዋል። አያ 54 ላይም ጌታችሁ በነፍሱ ላይ እዝነትን ጻፈ በማለት እዝነቱ በኋላ የመጣ መሆኑን ይናገራል ምክንያቱም ሳይጻፍ በፊት አልነበረምና። ከመጽጻፉ በፊት ላለመኖሩ ማስረጃው ምንድነው ከተባለ ጻፈ ተብሎ መነገሩ ሲሆን ይህ ሲፋት ተለይቶ ከሌሎች ሁሉ ፈጠረው(አላህ) ተብሎ ስለተነገረለት ነው። በመሆኑም የአላህ ራህመት ፍጡር መሆኑ በሃዲሳት ብቻ ሳይሆን በቁርአን በራሱም የተረጋገጠ እውነታ ነው። ሙስሊም ወገኖቻችን ታዲያ ያልትፈጠሩት የአላህ ሲፋትን ማለትም አልማኪር መሆን፣ አልፈታን መሆን። አደር መሆን ውዘተ ትተው ከተፈጠረው ከአላህ ባህርይ ጋር እንዲህ ግንኙነታቸውን ማጥበቃቸው ምንን ያመላክታል? ቢስሚ ላሂ አልማኪር አልፈታን አይሉም አራህማኒ አራሂም እንጂ!

እነዚህን በማጤን ላይ እያለን አላህ 99ኙን ምሕረት ለቂያማ ቀን አስቀምጦታል ይሉናል። አላህ የዚህን ሁሉ ሰው ሓጢአት(ሓጢአት በአላህ ዘንድ ባይታዎቅም) ችሎ የሚኖረው በአንዷ ክፍል ብቻ ከሆነ በ99ኙ ደሞ ከዚህ የበለጠ ቸርነት ማሳየት ሲገባው እናት ልጅን የማታይባት ቀን እና ሰዎችን የእሳት ሰንሰለት አዘጋጅቶ በቂጣቸው እያስገባ በአፋቸው የሚያወጣበት ዕለት ናት ቂያማ!(69:32 ተፍሲር ማንኛውም በተልይ ኢብኑ አባስ) ታዲያ የታለ 99ኙ ምሕረት አገልግሎት የሰጠው? አላህ ስለ ቁጣው እጅጉን ከመጨነቁ የተነሳኮ ጸሎቱ ራሱ ምሕረቴ ቁጣዬን በለጠች ምሕርቴ ቁጣዬን በለጠች ምሕረቴ ቁጣዬን በለጠች እያለ ነው። እስኪ የሚከተሉትን ታማኝ ምንጮች እንይ:-

جاء إذا حتى ،الملائكة عليه سلمت بسماء مر كلما كان به أسري لما وسلم عليه الله صلى النبي أن بلغني قال: رباح أبي بن عطاء عن - فقال ،عليه بالسلام فبدأه الملك ب(32 المختار أسرع. الشيء: إلى بدر)فبدره: فبدره ،عليه فسلم ملك هذا جبريل: له قال السادسة السماء فقال ،يصلي وجل عز الله إن جبريل: له قال السابعة السماء جاء فلما ،علي يسلم أن قبل عليه سلمت أني وددت وسلم: عليه الله صلى النبي غضبي. رحمتي سبقت ،والروح الملائكة رب ،قدوس سبوح يقول: قال: صلاته؟ وما قال: ،نعم قال: يصلي؟ أهو وسلم: عليه الله صلى النبي

(عب).

ከንዝ አል ዑማል (ፊ ሱናን አልአቅዋል ወላ ፋዕል) number 35457

ወደ ሰባተኛው ሰማይ በመጣ ጊዜ ጅብሪልን እንዲህ አለው:- አምላክ ይጸልያል?? ጂብሪልም አዎን አለው(ናዕም)። ጸሎቱ ምንድን ነው? አለ አለ ነቢዩ ጂብሪልም ክቡር ቅዱስ፡ የመላእክትና የመንፈስ ጌታ ከቁጣዬ በፊት ምሕረቴ ቀደመች እያለ ይጸልያል አለው። (የአላህ ጸሎት ምን እንደሆነ ልብ በሉልኝ) ተጨማሪ ማስረጃዎች ከታች ከነሊንኩ አስቀምጫለሁ:-

الله يصلي ؟ .. ماذا يقول ؟ .. و لمن يصلي ؟ .. و صلاته مثل صلاة محمد

هذا وفى حديث رواته ثقات لما وصلت إلى السماء السابعة قال لى جبريل عليه السلام رويدا أى قف قليلا فإن ربك يصلى قلت أهو يصلى وفى لفظ كيف يصلى وفى لفظ أخر قلت يا جبريل أيصلى ربك قال نعم قلت وما يقول قال يقول سبوح قدوس رب الملائكة والروح سبقت رحمتى غضبى ولا مانع من تكرر وقوع ذلك له صلى الله عليه وسلم من جبريل ومن غيره فى السماء السابعة وفيما فوقها لكن يبعد تعجبه صلى الله عليه وسلم من كونه عز وجل يصلى فى المرة الثانية وما بعدها.

وورد أن بنى إسرائيل سألوا موسى هل يصلى ربك فبكى موسى عليه الصلاة والسلام لذلك فقال الله تعالى يا موسى ما قالوا لك فقال قالوا الذى سمعت قال أخبرهم أنى أصلى وأن صلاتى تطفئ غضبى والله أعلم.

السيرة الحلبية في سيرة الأمين و المأمون .. باب ذكر الإسراء و المعراج

http://arabic.islamicweb.com/Books/seerah.asp?book=3&id=646

حدثنا أبو بكر بن أبي شيبة حدثنا محمد بن بشر العبدي حدثنا سعيد بن أبي عروبة عن قتادة عن مطرف بن عبد الله بن الشخير أن عائشة نبأته أن رسول الله صلى الله عليه وسلم كان يقول في ركوعه وسجوده سبوح قدوس رب الملائكة والروح

صحيح مسلم .. كتاب الصلاة .. باب ما يقال في الركوع و السجود

http://hadith.al-islam.com/Display/Display.asp?hnum=752&doc=1

This and in a hadith narrated by trustworthy people, when I reached the seventh heaven, Gabriel, peace be upon him, said to me slowly, “Stand a little, for your Lord is praying.” I said, “Does he pray?” And in another wording, “How does he pray?” And in another wording, I said, “O Gabriel, does your Lord pray?” He said: “Yes.” I said. My mercy is my wrath, and there is no objection to the repeated occurrence of that to him, peace and blessings of God be upon him, from Gabriel and others in the seventh heaven and above, but his amazement, may God’s prayers and peace be upon him, is far from the fact that he, the Mighty and Sublime, prays the second time and beyond.

And it was reported that the Children of Israel asked Moses, “Does your Lord pray?” Moses, peace and blessings of God be upon him, cried for that, so God Almighty said, “O Moses, what did they say to you?” He said, “They said that you heard.” He said, “Tell them that I pray and that my prayer extinguishes my anger. And God knows best.”

The Aleppo Biography in the Biography of Al-Amin and Al-Ma’mun. Chapter on the Remembrance of the Night Journey

ነቢዩ መሐመድ በአላህ መጸለይ ደንግጦ አዩሰሊ ረቡካ ማለትም ጌታህ ይጸልያል? ብሎ ሲጠይቅና አዎንታዊ ምላሽ ሲያገኝ እናዬዋለን። በመሆኑም አላሁ አዘውጀል ወተዓሊ ከፍተኛ የሆነ Anger management issue ወይንም ቁጣን የመቆጣጠር ከፍተኛ ችግር ውስጥ የነባ ሆኖ እናገኘዋለን። ጸሎቱ ሳይቀር ምሕረቱን የተመለከተ ነው እንደምናዬው!

ጉዳዩ ሲከፋ(Worsening the case scenario)

ከላይ ያየናቸው (6፡12, 54) እዝነትን በነፍሱ ላይ ጻፈ የሚለው አገላለጽ ምንን ያመለክታል? ቁርአን ውስጥ ተጻፈ የሚለው አገላለጽ ተደነገገ፣ ተወሰነ ወይም በነሱው አገላለጽ ተቀደረ ማለት ሲሆን አላህ ከቀደረው ወይም ከጻፈው ነገር መውጣት የሚችል ማንም የለም ተብሎ ይታመናል። እስኪ ይህ አገላለጽ (ጻፈ፣ ተጻፈ የሚለው) ድንጋጌ መሆኑን እንይ፡-

የላሚቱ ምዕራፍ አያ 180(2፡180)

كُتِبَ عَلَيْكُمْ إِذَا حَضَرَ أَحَدَكُمُ الْمَوْتُ إِن تَرَكَ خَيْرًا الْوَصِيَّةُ لِلْوَالِدَيْنِ وَالْأَقْرَبِينَ بِالْمَعْرُوفِ ۖ حَقًّا عَلَى الْمُتَّقِينَ

አንዳችሁን ሞት በመጣበት ጊዜ ሀብትን ቢተው ለወላጆችና ለቅርብ ዘመዶች በበጎ መናዘዝ በናንተ ላይ ተጻፈ።። (ይህ) በጥንቁቆቹ ላይ እርግጠኛ ድንጋጌ ተደነገገ።።

በተጨማሪም 178፣ 235 ሕግ ሲሰጥ ተጻፈ ይላል።

78፡29

وَكُلَّ شَيْءٍ أَحْصَيْنَاهُ كِتَابًا

ነገሩንም ሁሉ የተጻፈ ሲኾን አጠቃለልነው፡፡

ከእነዚህና መሰል አያዎች እንደምንረዳው ተጻፈ የሚለው ቃል ድንጋጌን ወይም ሕግን መመሪያን ወዘተ የሚመለከት መሆኑን ነው። በርግጥ ቃሉ ሌላ ትርጉሞች ይኖሩታል ግን ቁርአን ውስጥ እንደምናዬው ሕግን ድንጋጌን ወዘተ የሚመለከት ነው። ስለዚህ አላህ በነፍሱ ላይ በጻፈው ነገር ተገዢ ሆኖ ይኖራል ማለት ነው። ኢይይይ አላህ ለራሱ ቃል በነፍሱ ላይ ለጻፈው ነገር አይግዛም ከተባለ ደሞ ቃሉን የማያከብር ቋሚ ማንነት የሌለው እንደፈለገ መቀያየር የሚችልና በነፍሱ ላይ የተለያዩ ነገሮችን የሚጽፍ ያደርገዋል። የትኛው ነው አላህ ያ ሙስሊሚን? አላህ በነፍሱ ላይ ለጻፈው ነገር ሲግዛ ይኖራል ወይስ እንደፈለገ በመቀያየር ቋሚ ማንነት አልባ ሆኖ ይኖራል? (በነፍሱ ጻፈው ሲል አላህ ነፍስ አለው ወይ? የሚለው ይቆየንና ማለት ነው)።

ሌላ ሌላ ብንጨምር ከአሁኑ የበለጠ አዕምሯዊ ቁርጠት ይይዛቸዋልና ወገኖቻችን ለእነሱው ጤና በማሰብ እዚህ ላይ እናቁመው። ሲበዛም አንዱንም ሳይመልሱ ይቀራሉና ማለት ነው። እባካችሁ እንደው በምታምኑት ምንም ይሁን ምን ይሁንባችሁ መልስ ከመስጠታችሁ በፊት መጀመሪያ ጥያቄውን ተረዱት እባካችሁ። ስለ ድንጋይ ተጠይቃችሁ ስለ ላም አታውሩ ብሊዝዝዝ።

መድምደሚያ፡-

1. የአላህ ራህመት ወይም እዝነት ፍጡር ነው
2. አላህ በባሕርይው ብስጩና ቁጡ ነው
3. አላህ የተፈጠረውን ባህርይ ከሌሎቹ ዘለአለማዊ ባሕርያቱ ይልቅ አብልጦ አስተዋውቆታል
4. አላህ በነፍሱ ላይ ለጻፈው ነገር ሲገዛ በመኖር የራሱ እስረኛ ሆኗል ወይንም በነፍሱ ላይ የተለያዩ ነገሮችን በመጻፍ ቋሚ ማንነት የሌለው አካል ሆኗል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ወለወላዲቱ ድንግል ወለመስቀሉ ክቡር ይቆየን!